ቤተ መጻሕፍት

# መጽሐፈ ፡ ሕዝቅኤል ።

ከትርጓሜው ፡ ጋራ ፡

ንባቡ ፡ በግእዝ ፡ ትርጓሜው ፡ ባማርኛ ፡

ከኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ ተጽፎ ፡

ታተመ ።

፲፱፻፲፮

www.ethiopianorthodox.org



የኢትዮጵየ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ እንደራሴ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ።

## እኔ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ።

## ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ያሳተምሁበትን ፡ ምክንያት ፡ ማስታወቂያ ።

---

ስለ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ንባብና ፡ ትርጓሜ ፡ ነገር ፡ በቀድሞ ፡
ዘመን ፡ የተጻፉትን ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍት ፡ ስናነብና ፡ መምሕራን ፡
ያስ
ቃል ፡ ለቃል ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣውን ፡ ነገር ፡ ሲነግሩን ፡ እጅግ ፡ ያስ
ደንቃል ። በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ ከሙሴ ፡ ጀምሮ ፡ እስራኤል ፡ ተማር
ከው ፡ ከሔዱበት ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እስኪመለሱ ፡
ድረስ ፡ መጻሕፍተ ፡ ብሉይን ፡ ለማግኘትና ፡ ለማንበብ ፡ እጅግ ፡ ች
ግር ፡ ነበረ ። እነዚህም ፡ የብሉይ ፡ መጻሕፍቶች ፡ የሚገኙት ፡ በኢ
የሩሳሌም ፡ በትልቁ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በየሀገርም ፡ ውሥጥ ፡ በዋና ፡
በዋና ፡ ምኵራብ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ በሁሉ ፡ አይገኙም ፡ ነበር ።

የፋርስና ፡ የባቢሎንም ፡ ነገሥታት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እየዘ
መቱ ፡ ሕዝቡንና ፡ ካህናቱን ፡ ሲገድሉና ፡ ሲማርኩ ፡ መጻሕፍቱን
ም ፡ አቃጥለዋቸው ፡ ነበረና ፡ እስራኤል ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ አ
ዝነው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢያለቅሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልአኩ
ን ፡ ወደ ፡ ዕዝራ ፡ ልኮ ፡ የመጻሕፍተ ፡ ብሉይን ፡ ንባብና ፡ ትርጓሜ ፡
ገለጸለት ። ዕዝራም ፡ መጻሕፍተ ፡ ብሉይን ፡ በልቡ ፡ እያሰበ ፡ በቃ
ሉ ፡ እየተናገረ ፡ አስጥፎአቸዋል ። መጻሕፍተ ፡ ብሉይ
ም ፡ ለጊዜው ፡ የታጡበትና ፡ የጠፉበት ፡ ምክንያት ፡ ንባባቸውና ፡
ትርጓሚያቸው ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ስለሆነ ፡ በእጅ ፡ ጽፈት ፡ ብዙ ፡ መ
ጻሕፍትን ፡ ለመጻፍ ፡ አልተቻለም ፡ ነበረና ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡
ዛሬ ፡ ዘመን ፡ የጽፈት ፡ መኪና ፡ በነበረ ፡ ከብዛት ፡ የተነሣ ፡ ምንም ፡
ቢሆን ፡ መጻሕፍተ ፡ ብሉይ ፡ አይጠፉም ፡ ነበር ። እንሆ ፡ አሁን ፡
ዛሬ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ማንም ፡ የክርስቲያን ፡ ጠላት ፡ የሆነ ፡ ንጉሥ ፡
ቢነሣ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ጨርሶ ፡ ለማጥፋት ፡ አይችልም ።
አለመቻሉም ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ ተገልብ
ጠው ፡ በብዙ ፡ ታትመው ፡ በሁሉ ፡ ስፍራ ፡ የሚገኙ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ብ ፡ ያደርጉታል ።

፳፭ ፤ ወይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ እንተ ፡ ወሀብክዋ ፡ ለያዕቆብ ፡ ቍልዒየ ፡ ኀበ ፡ ነበሩ ፡ ባቲ ፡ አበዊክሙ ።

ለባሪያዬ ፡ ለያዕቆብ ፡ በሰጠኋት ፡ አባቶቻችሁ ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ በነበሩባት ፡ ምድር ፡ ይኖራሉ ። በያዕቆብ ፡ አዳምን ፡ በምድረ ፡ ርስት ፡ መንግሥት ፡ ሰማይን ፡ መናገር ፡ ነው ።

ወይነብሩ ፡ ላዕሌሃ ፡ እሙንቱ ፡ ወደቂቆሙ ፡ ወደቂቀ ፡ ደቂቆሙ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።

ክርሳቸውም ፡ በኋላ ፡ ልጆቻቸው ፡ የልጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ ለዘላለም ፡ ይኖሩባታል ።

ወዳዊት ፡ ገብርየ ፡ መልአክሙ ፡ ለዓለም ።

ዘሩባቤል ፡ ክርስቶስ ፡ ለዘላለም ፡ አለቃቸው ፡ ሁኖ ፡ ይኖራል ፡ አለ ። ለዓለም ፡ ማለት ፡ ወርቁን ፡ እንጂ ፡ ሰሙን ፡ አይሻም ፤ ወይነግሥ ፡ ለቤተ ፡ ያዕቆብ ፡ ለዓለም ፡ ወአልቦ ፡ ማኅለቅት ፡ ለመንግሥቱ ፡ እንዳለ ፡ ( ሉቃ ፩ ፡ ፴፫ ) ።

፳፮ ፤ ወእትካየድ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ኪዳነ ፡ ሰላም ።

ምስሌሆሙ ፡ ለማለት ፡ ደገመው ፡ ( ም ፴፬ ፡ ፳፭ ) ።

ወይከውኖሙ ፡ ኪዳነ ፡ ዘለዓለም ።

ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ የማይፈርስ ፡ የማይለወጥ ፡ ይሆንላቸዋል ፡ ( ኤር ፴፩ ፡ ፴፩—፴፫ ) ።

ወእሠርዖሙ ፡ ወአበዝኖሙ ።

በምድረ ፡ ርስት ፡ እተክላቸዋለሁ ፡ እንደቀድሞ ፡ አበዛቸዋለሁ ። በ ፤ ሁሉንም ፡ ልጆቼ ፡ እላቸዋለሁ ፡ ( ሮሜ ፰ ፡ ፳፱ ) ።

ወእሬሲ ፡ መቅደስየ ፡ በማእከሎሙ ፡ ለዓለም ።

መቅደሴን ፡ ለዘላለም ፡ በመካከላቸው ፡ አደርጋለሁ ።

፳፯ ፤ ወይከውን ፡ ማኅደርየ ፡ ላዕሌሆሙ ።

ልቡናቸውን ፡ ዠፋን ፡ ሰውነታቸውን ፡ ድንኳን ፡ አድርጌ ፡ አድርባቸዋለሁ ፡ ( ዮሐ ፲፬ ፡ ፳፫ ) ።

ወእከውኖሙ ፡ አምላኮሙ ፡ ወእሙንቱ ፡ ይከውኑኒ ፡ ሕዝብየ ።



እንዳለፈው ፡ ( ቍ ፳፫ ። ራእ ፳፩ ፡ ፫ ) ።

፳፰ ፤ ወየአምሩ ፡ አሕዛብ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአቄድሶሙ ፡ ለእስራኤል ።

አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ እስራኤልን ፡ የማከብራቸው ፡ እኔ ፡ እንደሆንሁ ፡ ያውቃሉ ።

ሶበ ፡ ኮነ ፡ መቅደስየ ፡ ማእከሎሙ ፡ ለዓለም ።

መቅደሴ ፡ ለዘላለም ፡ በመካከላቸው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አለ ፤ በመቅደሰ ፡ ኦሪት ፡ መቅደሰ ፡ ወንጌልን ፡ መናገር ፡ ነው ። ምድረ ፡ ርስትን ፡ መቅደሰ ፡ ኦሪትን ፡ ለዓለም ፡ አይለውምና ።

---

## ምዕራፍ ፡ ፴፰ ።

፩ ፤ ወኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀቤየ ፡ እንዘ ፡ ይብል ።

ቃለ ፡ እግዚ ፡ ወደኔ ፡ መጣ ፡ ተነገረ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ።

፪ ፤ ወልደ ፡ እጓለመሕያው ፡ ሚም ፡ ገጸከ ፡ ላዕለ ፡ ጎግ ፡ ወምድረ ፡ ማጎግ ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ገጸ ፡ ትንቢትህን ፡ ወደጎግ ፡ መልስ ፤ በማጎግ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ አጽና ፡ አለ ፤ ጎግ ፡ ንጉሡ ፡ ማጎግ ፡ ሕዝቡ ፡ ናቸው ።

መልአከ ፡ ወርእሰ ፡ ሞሳሕ ፡ ወቶቤል ።

መልአክና ፡ ርእስ ፡ የተደራረበ ፡ ነው ፤ ኅሩያን ፡ ወሠናያን ፡ ሊባኖስ ፡ እንዳለ ፡ ( ፴፩ ፡ ፲፯ ) ። መልአከ ፡ ሞሳሕ ፡ ወርእሰ ፡ ቶቤል ፡ ብሎ ፡ ይገጥሟል ፤ ጎግን ፡ የሞሳሕና ፡ የቶቤል ፡ አለቃ ፡ አለው ። በ ፤ ዋዌውን ፡ ትቶ ፡ መልአከ ፡ ርእሰ ፡ ሞሳሕ ፡ ወቶቤል ፡ ይላል ፡ ያለቃቸው ፡ አለቃ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ንጉሡ ፡ ነገሥታቸው ፡ እርሱ ፡ ነውና ። ማጎግና ፡ ሞሳሕ ፡ ቶቤል ፡ ወንድማማቾች ፡ ናቸው ፡ ከ ፺ ቱ ፡ ደቂቀ ፡ ያ

www.ethiopianorthodox.org

ወበእንተዝ ፡ ርሕበ ፡ ቤት ፡ እምላዕሉ ።
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በስተላይ ፡ በስተውጭው ፡ ሰፊ ፡ ታላቅ ፡ ሆነ ።

ወከማሁ ፡ እምታሕቱ ፡ ያዐርግ ፡ ኀበ ፡ መልዕልት ፡ በማእከሉ ።
እንደስፋቱ ፡ መጠን ፡ ዕርከኑ ፡ መሰላሉ ፡ በዕቃ ፡ ቤቱና ፡ በመቅደሱ ፡ መካከል ፡ ከታች ፡ ወደላይ ፡ ያወጣል ።

፰ ፤ ወርኢኩ ፡ ለቤት ፡ ልዕልናሁ ፡ በኵሉ ፡ ዐውዱ ።
በዙሪያው ፡ ሁሉ ፡ የመቅደሱን ፡ ስፋት ፡ ልዕልናውን ፡ አየሁ ፡ ተመለከትኁ ፡ አለ ። ከመሠረቱ ፡ እስከጕልላቱ ፡ ፻ክንድ ፡ ነውና ፤ በታሪክ ፡ እንደተጻፈ ። በ ፤ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ከፊተኛው ፡ መቅደስ ፡ መብለጡን ፡ ክብሩን ፡ ቅድስናውን ፡ አየሁለት ፡ ሲል ፡ ነው ። እንደፊተኛው ፡ ጣዖት ፡ አልቆመበትም ፤ ኋላም ፡ አምላክ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ ታይቶበታል ፡ በቃል ፡ ሰብአዊ ፡ አስተምሮበታልና ። የዐቢ ፡ ክብሩ ፡ ለዝንቱ ፡ ቤት ፡ ደኃራይ ፡ እምቀዳማይ ፡ ካለው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ( ሐጌ፪ ፡ ፱ ) ፤ አይሁድ ፡ ግን ፡ ሄሮድስ ፡ ስላስጌጠው ፡ ይላሉ ።

ወመሠረተ ፡ ገበዋት ፡ ምሉዐ ፡ ህለት ፡ ስድስ ፡ በእመት ፡ ዐቢይ ።
የዕቃ ፡ ቤቶቹ ፡ መሠረት ፡ በታላቅ ፡ ክንድ ፡ ፮ ክንድ ፡ በዘንጉ ፡ ምሉ ፡ ዘንግ ፡ ነው ። እመት ፡ ወጥፍሕ ፡ ያለውን ፡ እመት ፡ ዐቢይ ፡ ብሎ ፡ አመጣው ፡ ( ም ፵ ፡ ፭ ) ።

፱ ፤ ወርሕበ ፡ አረፍት ፡ ዘገበዋት ፡ እምአፍአ ፡ ሐምስ ፡ በእመት ።
የናሱ ፡ ወርድ ፡ ግን ፡ በአፍአ ፡ ፭ክንድ ፡ ነው ፡ አለ ። ምሉዐ ፡ ህለት ፡ ካለው ፡ አንዱ ፡ ክንድ ፡ ወደርሕበ ፡ ገቦ ፡ ሒዶ ፡ ለጕርጆቹ ፡ ማሰማሚያ ፡ ሁኑዋል ።

ወሙናሐ ፡ ቤት ፡ በገበዋተ ፡ ቤት ።
መዛነቢያው ፡ ፈሰሱ ፡ በቤቱ ፡ ዙሪያ ፡ ነው ።

፲ ፤ ወማእከለ ፡ ኤስኬዴሬያት ፡ ርሕቡ ፡ ፳ በእመት ፡ የዐውዶ ፡ ለቤት ፡ ዐውደ ፡ ዐውዱ ።
በመቅደሱ ፡ ዕቃ ፡ ቤትና ፡ በወዲያኛው ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ በቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ዙሪያ ፡ በሦስቱ ፡ ማዕዝን ፡ ፳፳ክንድ ፡ ወልወል ፡ አለ ።



፲፩ ፤ ወኖኅተ ፡ ገቦ ፡ ለሙናሕ ።
የመቅደሱ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ደጆች ፡ አፉ ፡ ወደፈሰሱ ፡ ነው ።

አሐቲ ፡ ኖኅት ፡ ፍኖተ ፡ ሰሜን ።
አንዲቱ ፡ በሰሜን ፡ እኩል ፡ ናት ፡ ወደሰሜን ፡ ታያለች ።

ወአሐቲ ፡ ኖኅት ፡ ለደቡብ ።
አንዲቱ ፡ በደቡብ ፡ እኩል ፡ ናት ፡ ወደደቡብ ፡ ታያለች ።

ወርሕበ ፡ መካነ ፡ ሙናሕ ፡ ሐምስ ፡ በእመት ፡ ዐውደ ፡ ዐውዱ ።
በመቅደሱ ፡ ዙሪያ ፡ ያለው ፡ የፈሰሱ ፡ ቦታ ፡ ስፋቱ ፡ ፭ ክንድ ፡ ነው ። ሙናሕ ፡ የዕብራይስጥ ፡ ቃል ፡ ነው ፤ መዛነቢያ ፡ ፈሰስ ፡ ስብሳብ ፡ ማረፊያ ፡ ማሳረፊያ ፡ ጥግ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ መሠረቱን ፡ ለማጽናትና ፡ ውሀ ፡ እንዳይገባ ፡ ለመግታት ፡ በታላላቅ ፡ በሰፋፊ ፡ ደንጊያ ፡ ተጸፍጽፏል ።

---

ከምዕ ፵ ፡ ቍ፵፫ ፡ ዠምሮ ፡ እስከዚህ ፡ ያለውን ፡ ንባብና ፡ ትርጓሜ ፡ ይህ ፡ ሦስተኛው ፡ ሥዕል ፡ ፈጽሞ ፡ ያስረዳል ፤ የኡላሙና ፡ የመቅደሱ ፡ የዕቃ ፡ ቤቱና ፡ የፈሰሱ ፡ ሥራቸው ፡ እንደዚህ ፡ ነውና ። ምልክቱ ፡ በቶሎ ፡ እንዲገኝ ፡ ፊደሉ ፡ በፊደል ፡ ተተርጕሞ ፡ ንባቡ ፡ በአኀዝ ፡ ተቈራኝቷል ። የፊደሉ ፡ ተራ ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ ይመራል ፡ አያሳስትም ፤ ሥዕሉም ፡ እንደጽሑይ ፡ መጽሔት ፡ ምሥጢሩን ፡ ገልጦ ፡ ንባቡን ፡ አስጊጦ ፡ ያሳያል ። በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሥዕሎች ፡ ሁሉም ፡ ጥንታውያን ፡ ናቸው ፤ ይልቁንም ፡ የአዕፃዳቱና ፡ የምሥዋዑ ፡ የመቅደሱና ፡ የመበኡ ፡ ንድፍ ፡ በነቢዩ ፡ በሕዝቅኤል ፡ እጅ ፡ ከተሣለው ፡ ከጥንታዊው ፡ ሥዕል ፡ ተቀድቶ ፤ እንደመጽሐፉ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ ሲያያዝ ፡ መጥቷል ። ሕዝቅኤልም ፡ በራእይ ፡ ያየውን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሥሎ ፡ መስሎ ፡ ጽፎ ፡ ነድፎ ፡ ለሕዝቡ ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፤ ሕዝቡም ፡ ይማሩት ፡ ያስተምሩት ፡ ጠብቀው ፡ ያኖሩት ፡ ዘንድ ፡ ጌታ ፡ እንዳዘዘ ፡ መጽሐፉ ፡ ይመሰክራል ፡ ( ም፵፫ ፡ ፲፩ ) ።

www.ethiopianorthodox.org

፲ ፤ ወአንተ ፡ ወልደ ፡ እጓለመሕያው ፡ አግህድ ፡ ሎሙ ፡ ለቤተ ፡ እስ
ራኤል ፡ ዘንተ ፡ ቤተ ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ይህነን ፡ ቤት ፡ ለቤተ ፡ እስራኤል ፡ ገ
ልጸህ ፡ አስረድተህ ፡ ንገራቸው ።

ወይትኀፈሩ ፡ እምኀጣውኢሆሙ ።

ከኀጢአታቸው ፡ የተነሣ ፡ ይፈሩ ፡ ከጥፍራቸው ፡ ይጓቡ ። የ
ኋለኛውን ፡ ሲነግራቸው ፡ የፊተኛውን ፡ ያስባሉና ።

ወይመጥኑ ፡ አምሳሊሁ ።

ልኩን ፡ ያስተውሉ ፡ ይመልከቱ ።

፲፩ ፤ ወለእመ ፡ ተኀፍሩ ፡ እምኵሉ ፡ ዘገብሩ ፡ አይድዖሙ ፡ ሥዕለ ፡ ዝን
ቱ ፡ ቤት ።

የፊተኛው ፡ መቅደስ ፡ የፈረሰ ፡ በኃጢአታችን ፡ እንጂ ፡ ነው ፡
ቢሉ ፡ ሥራውን ፡ ንገራቸው ፡ ንድፉን ፡ አሳያቸው ።

ወአምሳሊሁ ፡ ወሙብአቲሁ ፡ ወሙፃአቲሁ ።

አሠራረዙን ፡ አቀራረፁን ፤ መውጫ ፡ መግቢያውን ፡ ሁሉ ።

ወኵሎ ፡ ሥዕሎ ።

ሥዕሉን ፡ ሥዕልነቱን ፡ አለ ፤ ላለፈው ፡ የመቅደሰ ፡ ሰሎሞን ፡
ለሚመጣው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አምሳል ፡ መሆኑን ።

ወኵሎ ፡ ትእዛዞ ፡ ወኵሎ ፡ ሥርዓቶ ፡ ወኵሎ ፡ ሕጎ ።

በውስጡ ፡ የሚደረገውን ፡ ትእዛዝ ፤ ሕጉን ፡ ሥርዓቱን ፡ ሁ
ሉ ፡ ንገራቸው ፡ አስተምራቸው ። ትእዛዝ ፡ አድርጉ ፡ አድ
ርጉ ፡ የሚለው ፤ ሕጓ ፡ አታድርጉ ፡ የሚለው ፡ ነው ። ሥ
ርዓት ፡ ጓን ፡ ከሕጓ ፡ ተወልዶ ፡ በትእዛዝ ፡ የሚያድጓ ፡ ንጹ
ሕ ፡ ውሳኔ ፡ ርቱዕ ፡ ብያኔ ፡ ነው ፤ ሁለቱንም ፡ ያስተባብራል ።

ወጸሐፎ ፡ በቅድሜሆሙ ።

እያዩህ ፡ በፊታቸው ፡ ጻፈው ፡ አለ ፤ በጽሕፈት ፡ አንጻህ ፡ ቀ
ርፀህ ፡ ሥለህ ፡ መስለህ ፡ አሳያቸው ፡ ንድፉን ፡ ቢጋሩን ፡ ስ
ጣቸው ፡ ሲለው ፡ ነው ። ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ንሣእ ፡ ጓንፋለ ፡ ወ
ሠዐል ፡ ላዕሌሃ ፡ እንዳለው ፡ አይዶለም ፡ ( ም፬ ፡ ፩ ) ፤ በቁ



ሙ ፡ እንደብልህ ፡ ገበዝ ፡ አምባ ፡ ሥሎ ፡ መስሎ ፡ ነድፎ ፡
በጓሮ ፡ ማሳየት ፡ ሰፍሮ ፡ ቈጥሮ ፡ መስጠት ፡ ነው ፡ እንጂ ።
መልአኩ ፡ ለርሱ ፡ ጠንቅቆ ፡ እንዳሳየው ፡ እርሱም ፡ ለሕዝ
ቡ ፡ ጠንቅቆ ፡ ያሳያል ፡ ( ም፵ ፡ ፬ ) ።

ወይዕቀቡ ፡ ኵሎ ፡ ሥዕሎ ፡ ወትእዛዞ ።

ሥዕሉንና ፡ ትእዛዙን ፡ ካንተ ፡ ይማሩ ፤ ጠብቀው ፡ ያኑሩ ።

ወይጓበርዎ ።

ኋላ ፡ በሚጠት ፡ ይህን ፡ አስመስለው ፡ ይሥሩ ።

፲፪ ፤ ወዝንቱ ፡ ሕጉ ፡ ለቤት ፡ ዘዲበ ፡ ርእሰ ፡ ደብር ።

በተራራው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሕጓ ፡ ይህ ፡
ነው ፡ አለ ፤ ዝንቱ ፡ ያለፈውም ፡ የሚመጣውም ፡ ነው ።

ወኵሉ ፡ ጽንፉ ፡ ዐውደ ፡ ዘየዐውድ ፡ ቅዱሰ ፡ ቅዱሳን ።

በመቅደሱ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉ ፡ የዐዐድ ፡ ጸናፊና ፡ የዐፀድ ፡ ውሳ
ጢ ፡ ሥርዓት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ናሁ ፡ ዝንቱ ፡ ሕጉ ፡ ለቤት ።

ዝንቱና ፡ ዝንቱ ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ ለአጽንዖተ ፡ ነገር ፡ ደገመ
ው ። ። ምሳሌውን ፡ ምሳሌነቱን ፡ ከዚህ ፡ ይናገራሉ ፤ ፺
ው ፡ ክንድ ፡ ሁል ፡ በዙሪያቸው ፡ ያሉ ፡ የአሕዛብ ፤ የአፍአ ፡
ቅጽር ፡ የሕዝቡ ፤ የውስጥ ፡ ቅጽር ፡ ለእጓዚ ፡ ለቤተ ፡ መቅደ
ስ ፡ የሚቀርቡ ፡ የካህናቱ ፤ ዕርከን ፡ የማዓርጋቸው ። በሦስ
ቱ ፡ ማዕዝን ፡ በአፍአ ፡ በውስጥ ፡ ያሉ ፡ ፳ቱ ፡ ደጅ ፡ አፎች ፡
የ፳ቱ ፡ አበው ፤ በአፍአ ፡ ያሉት ፡ የሴም ፡ የካም ፡ የያፌት ፤
በውስጥ ፡ ያሉት ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ። ከነዚ
ሁም ፡ በመቅደሱ ፡ አንጻር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያሉት ፡ ሁለ
ቱ ፡ የምሥራቅ ፡ ደጆች ፡ የሴምና ፡ የይስሐቅ ፡ ምሳሌ ፡ ናቸ
ው ፤ ብርሃን ፡ በነዚህ ፡ መጓባቱ ። ይትባረክ ፡ እጓዚአብሔ
ር ፡ አምላኩ ፡ ለሴም ፡ ወይኅድር ፡ በሐይመተ ፡ ሴም ፤ እም
ይስሐቅ ፡ ይሰመይ ፡ ለከ ፡ ዘርዕ ፡ ተብሎ ፡ ከተነገረላቸው ፡ እ
ንዲወለድ ፡ ያሳያል ፡ ( ዘፍ፱ ፡ ፳፮—፳፯ ። ዘፍ ፳፩ ፡ ፲፪ ) ።
ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የነቢያት ፤ ፫ ክፍል ፡ መሆኑዋ ፡ በሦስቱ ፡ ክ



www.ethiopianorthodox.org

